ቅዱስ ጳውሎስ ማነው?

እግዚአብሔር ወንጌልን ለዓለም ያዳርሱ ዘንድ ለአገልግሎት ከመረጣቸው ታላላቅ ሰዎች አንዱና ዋነኛው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ ይህ ሐዋርያ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል የተመረጠ አልነበረም፡፡ እንዲያውም፤ አስቀድሞ ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረ እና ብዙዎች የሚፈሩት - በአይሁድ ስሙ ‹ሳውል›፤ በሮማዊ ስሙ ደግሞ ‹ጳውሎስ› ይባል የነበረ ለእሥራኤል ሃይማኖትም ቀናኢ የነበረ ሰው ነበር፡፡ ወላጆቹ ከብንያም ነገድ የተገኙ አይሁዶች ሲሆኑ፤ እርሱም ለሃይማኖቱ ቀናኢ እንዲሆን በማለት የአይሁድን ትምህርት እንዲማር አድርገዋል፡፡ ይህንን ትምህርት በወቅቱ ከነበረው እጅግ ታላቅ የአይሁድ መምህር ረቢ ገማልያል ሥር መማር ችሏል፡፡ እርሱም እንደ መምህሩ ገማልያል ፈሪሳዊ ሆኖ ለአይሁድ ሃይማኖትና ለሕግጋቶቹ እጅግ የሚጠነቀቅ ሰው ሊሆን ችሏል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ሲሰማ ከዚህ ቀደም እስራኤላውያን በሐሰተኛ እምነቶች የተታለሉበት ጊዜ በማሰብ እምነቱን ለማጥፋት ቆርጦ ተነሳ፡፡ ዋናውን ተልእኮውም ክርስቲያኖችን ማሳደድና ማጥፋት አድርጎ ስሙ እጅግ የሚፈራና በክርስቲያኖች ላይ መከራን እጅጉን የሚያበዛ ሰው ሆነ፡፡ ሆኖም ግን፤ እግዚአብሔር ለሌላ ተልእኮ መርጦት ነበርና፤ በዚህ ክፉ መንገድ ሊገፋ አልቻለም፡፡ የእርሱ ታሪክ በዝርዝር በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ተቀምጧል፤ እንዲህ ሲል፡-

> “ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት ሄደ፥ በዚህ መንገድ ያሉትንም ሰዎች ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ፥ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኩራቦች ደብዳቤ ከእርሱ ለመነ። ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ፤ በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ። ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አለው። እርሱም። አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው። እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ። ጌታ ሆይ፥ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም። ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው። ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁን እየሰሙ ማንን ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቁመው። ሳውልም ከምድር ተነሣ፥ አይኖቹም በተከፈቱ ጊዜ ምንም አላየም፤ እጁንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አገቡት። ሳያይም ሦስት ቀን ኖረ፤ አልበላምም አልጠጣምም።” (ሐዋ 9፡1-9)

በዚህ መልክ እጅግ ይፈራ የነበረው የክርስቲያኖች አሳዳጅ፤ በኋላ ላይ ሙሉ ሕይወቱን ለክርስቶስ አሳልፎ የሰጠ ሐዋርያ ሆነ፡፡ ተልእኮውንም በከፍተኛ ትጋት ይፈጽም ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ በወቅቱ ኃያል በነበረችው በሮም ከተማ ውስጥ ወንጌል እንዲስፋፋ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ተግቶ የሠራና የተሳካለት የለም፡፡ የሐዋርያት ሥራ በብዛት የቅዱስ ጳውሎስን የወንጌል አገልግሎት መተረኩ፤ ከሐዲስ ኪዳን ውስጥም ቅዱስ ጳውሎስ ሃያ ሁለት በመቶውን መጻፉን ስንመለከት ምን ያህል ተጽእኖ ማሳደር እንደቻለ መገንዘብ እንችላለን፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለቅዱስ ጳውሎስ እጅግ ከፍተኛ አክብሮት ይሰጠዋል፡፡ አባቶቻችን ስሙንና ሥራውን በጎበረት አድርገው ሲተረጉሙ፤ እንዲህ ይላሉ፡፡ ጳውሎስ ማለት ብርሃን ማለት ነው -የሰውን ውስጣዊ አእምሮ ብሩህ ያደርጋልና፡፡ ጳውሎስ ማለት መዶሻ ነው - መዶሻ ሰባቱን ማዕድናት ቀጥቅጦ አንድ እንደሚያደርግ እርሱም ሰባቱን እርስ በእርስ የተቃረኑ ነገሮችን (ሰውና እግዚአብሔርን፣ ሰውና መላእክትን፣ ሕዝብና አሕዛብን፣ ነፍስና ሥጋን) አንድ አድርጎ አስታርቋልና፡፡ ጳውሎስ ማለት ብረት ነው፤ ብረት የማይገባበት እንደሌለ እርሱም ከሥጋዊም ከመንፈሳዊም እየገባ ይጽፋልና፡፡ ጳውሎስ ማለት ወርቅ ብር ነው - እርሱም ለቤተክርስቲያን እንዲሁ ነውና፡፡ እንዲህና ከዚህም በላይ በሆነ መንገድ ስሙን ከሥራው እያስተባበሩ እያመሰገኑ ይናገሩለታል፡፡